# ውድ ዋቻሞ አታሮ፤

አንዱ ዓለም ተፈራ

ያቀረቡትን ጽሑፍ ቀደም ብዬ አንብቤዋለሁ። ( በአሲምባ ድረገፅ ) ነገሩ በተወሰኑ ግለሰቦች አኳኃን የታዩ ሀቅ ስለሆነ፤ ምንም ዓይነት ማስተባበያ መሥጠት አይቻልም። ሁለት ነገሮች ግን ግልጽ መሆን አለባቸው። በመጀመሪያ ይህ የቀረበው ጉዳይ ግለሰቦችን የሚመለከት እንጂ መላ የታጋዩን ክፍል የሚመለከት አይደለም። እናም እንዲህ አጠቃሎ ማቅረቡ ሙሉ አያደርገውም። አስፈላጊም ከሆነ፤ ትግሉን ወደፊት ለማራመድ፤ የተሞከርሩትን ጥረቶችና በእምቢተኝነት ወይንም በመሸሽ የራቁትን በስም በመጥቀስ ማቅረብ ያስፈልግ ነበር። እንዲሁ በጅምላ የምናደርገው ወቀሳ ማንንም አይረዳም። ቀጥሎ ደግሞ "እኔ ብቻ ነኝ ጥረት የማደርገው፤ ሌሎቹ ሸሹ!" ከሚለው በመነሳት ሳይሆን፤ "እኔም ዝግጁ ነኝ ለመተባበር!" ከሚለው ተነስቶ ሌሎችን መቅረብ ይረዳል።

ዋቻሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱ መምህር ሆኜ ከደርግ በፊት አስተምሬያለሁ። በጣም የምወዳት ከተማና ብዙ ታጋዮችን በወቅቱ የተገናኘሁባት ከተማ ናት። ስምዎ በትዝታ ወደዚያ ወቅትና ቦታ ወሰደኝ። እንግዲህ ጥረታችንን አስተባብረን ወደፊት የምንሄድበት መንገድ ካለ፤ እኔ ለመተባበር ዝግጁ ነኝ። በኔ እምነት፤ ሌሎች ይሄን ስላደረጉ ወይንም ስላላደረጉ ሳይሆን፤ እኛ ልናደርግ የምንፈልገውን እና የምንችለውን ማድረግ የራሳችን የትውልድ፣ የታሪክና የሀገር ተልዕኮ አለብን። እናም ሌሎችን በመውቀስ ሳይሆን እኛ ቀዳሚ ታጋዮች ሆነን በመገኘት እናስተባብር።

ከታላቅ የአክብሮት ሰላምታ ጋር

# <u>አገር ለማዳን የሚችል ድርጅት ለመፍጠር አለን የሚሉትን ሰዎች ስንቀርባቸው እሽ ይሉና ይሸሻሉ።</u>

ከዋቻሞ አታሮ

ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በመነሳት አገርን ከወያኔ ግዝገዛ ለማላቀቅ ከግለሰብ እስከ ሲቪክና የፖለቲካ ድርጅቶች ድረስ ወያኔን የመቃውሙ ጥረት የሚናቅ አይደለም። ዳሩ ግን ጥረቶቹ ሁሉ በሃቅ ከኢትዮጵያ፣ ከሕዝብና ከአገር ጥቅም አኳያ ጋር የተያያዙ ባለመሆናቸው የተበታተኑና ውጤት አልባዎች ናቸው። ይህን አገር ወዳዱ በደንብና በቅጡ ሊገነዘበው ያስፈልጋል።

ስለዚህ በተጨባጭ ሁኔታ ውጤት ለማምጣት ትግሉ በሕዝብ ትርታና በአገር ጥቅሞች ላይ ተመስርቶ የሕዝብ ብሔራዊ አለኝታን ያቀፈና በፅኑ ተደራጅቶ የቆመና አብሮ የድል ዋስትና ሆኖ የዘለቀ መሆን አለበት ተብሎ ገና ዱሮ በተደጋሚ ጥረት ጥያቄ ተደርጓል ።

ይህን መረሆ መሰረት በማድረግ ለአገር ወገን ብቁ ናቸው፣ይቆረቆራሉ ያደርጉታል ይጠቅማሉ በማለት የቀረብናቸው እሽ ይሉና ይሸሻሉ/ ትሸሻላችሁ ፣ታፈነግጣላችሁ  ለምን ? ምን ሰለሆነ ነው የምትሸሹት ? ነገር ግን በየመድረኩ፣ በየአደባባዮ ንግግሮችን፣በየሬድዎ ፣ በየፓልቶኩ ወዘተ ቃለ ምልልሶችን ትሰጣላትችሁ፣ የአገር ችግርን የሕዝብ ብሶት ትናገራላችሁ፣ ወያኔን ትረግማላችሁ፣ ታወግዛላችሁ  በአገር ጠላቶች ላይ ለመዝመት አንድነት ያለው በተግባር የሚገለጽ ሥራ ተደራጅተን ለማካሄድ ሲትጠየቀ የትብብር ፍላጐት እንዴ ሬት ይመርባችኋል ለምን ? ለትብብርና ለመደራጀት ፍርሃት የሆነው ምንድነው ? ከንቱ ትችትና ፕሮፓጋንዳ ብቻውን የትም አያደርሰንም።

በየሬድዎ በየፓልቶኩ ንግግርና ቃለ ምልልስ ሰታደርጉ ምን ፈልጋችሁ ነው ? እሽ ብላችሁ ከቀረባችሁ በኃላ መሸሹን ምን አመጣው ? እውነት ለአገር ወገን ትቆረቆራላችሁ ? ወይንስ ምን ? ለራስ ዝናና ስም ? ጠያቂዎች ጥያቄውን ስላቀረቡላችሁ ነው? ለአገር ወገን ፣ አገሩን ለአጣ ሕዝብ፣ ለታሪካዊ ኢትዮጵያ እውን ቆማችኋል?

ለአገር የሚሆን ጠንካራና ብርቱ ድርጅት እንፍጠር ተብሎ ከተቀራረብን በኃላ የተሰባሰብነውን እንዲንበታተን ማድረግ፣ራስን ማግለል፣ ግንኙነትን ማቋረጥ፣መሸሽና ማሸሽት፤ እየጀመሩ መተውና ሌላውን ተሰፋ ለማስቆረ መጣር፣ትግልን ማደናቀፍ በራሱ ስውር የጠላት ስራ ነው።እንደዚሁም በየቦታው እንደ ጉልት በጓደኛና በውዳጅ እየተቧደኑ የእኔ የእኛ ድርጅት ማለትና እንደ ብቸኛ በተናጠል የተራራ ቀበሮ (ወልፍ) አዳኝ በየሬደዎና

ፓልቶኮች እየተዘዋወሩ ሲጮኹና ሲያወሩ ቢውሉ፣እንደ ዋልያም ቋጥኝ ከቋጥኝ በተናጥል ቢዘለል ውጤታማ ለውጥ አመጣም።ጠላት  አይጐዳም። ቡፋ ፖለቲካ፣ተልካሻና መላቅጡ የጠፋበት ትግል የትም አያደርሰንም።

የአገር ፍቅር ማለት በድርጊት የሚገለጽ እንጂ በየፓልቶኩና ሬድዎ  ጣቢያዎች በሚሰጡ ንግግሮች፣ለብቸኛ ጥቅም፣ ለራስ ዝና ሳይሆን ለሕይወቱ ሳይሳሳ በቁርጠኝነትና በፅናት በአርአያነት መስዋዕት በመሆን ጠላትን ደምስሶ ሕዝብን ነፃ ማውጣት ነው።

ሰለዚህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋነኛ ትከረትና ጥቅም ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ስለሆነ ይህን ከማራመድ ወይንም ከመወጣት ረገድ ከሚደረጉት ቅስቀሳ  ትብብርና ትስስር እገዛ ረገድ ጠንካራና አሸናፊ ድርጅት እንፍጠር ነው። በግለሰብና በየቦታው በመልኰል በብትንና አናሳ ስብስቦች አገር አይጠበቅም።ይህ በመሆኑ አስንቆና አስደፍሮንም ጒድቶን ቆይቷል።

በእውነት ለአገር ወገን የምታስቡና የምትቆረቆሩ ተግባሬነው የምትሉ ፣ ለኢትዮጵያ ፣ ለኢትዮጵዊነትና ለሰንደቅ ዓለማ ከሆነ ጠንቀቅ ብሎ ልቦና ገዝቶ ሙያን በል አርጐ ትብብርንና አንድነትን  ከአንጀት ወገብን ጠበቅ አድርጐ ከአገር ልጆች ጋር ተሳስሮ ጠንካራና ብርቱ ድርጅትን ፈጥሮ በመምራትና በመታግል አመርቂ ሥራ በመስራት ወያኔን ከነምናምኑ በታትኖና ድራሹን አጥፍቶ የአገርን ትንሳኤ ማረጋገጥ ነው። ከዚህ ውጭ በየፓልቶክና ሬድዎ ንግግር፣ አፍራሽ ሸሽትና ፍርሃት ለአገር ወገን አይበጅም። ፊኒቶ !

## ትብብር የድል ዋስትና ነው ! ! !

## እንደራጅ ለአገር ወገን አለኝታ ! ! !